የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

ግንቦት 10 ቀን 2008 ዓ ም

# መግለጫ

ወያኔ / ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሌት ተቀን ከሚፈጽመዉ ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀዉስ ባሻገር ብሄሮች ለዘመናት ተጋብተዉ፡ተዋልደዉና ተከባብረዉ የኖሩባትን ሀገር ዛሬ በዘር በሀይማኖት በክልልና በጎጥ እንድንከፋፈል በማድረግ እርስ በራሳችን እንዳንፋቀር እንዳንስማማና ተባብረን ሀገራችንን እንዳናለማና እንዳናበለጽግ ዘረኝነትን አስፋፍቶ የእርስ በርስ ግጭቶችን በማራገብ ላይ ይገኛል ።

ይህ አንድነታችን የማዳከሚያና የመከፋፈያ ብሎም የስልጣን ማራዘሚያ ዘዴዉ አልበቃ ብሎ ፤ህዝባችን ተስፋፊና ወራሪወችን ባይበገሬ ክንዱ ድባቅ እየመታ ለረጅም ዘመናት በአጥንቱና በደሙ አስክብሮ ያቆያት እናት ሃገራችን ዘላቂ ብሄራዊ ጥቅሟን በሚጎዳ መንገድ ዳር ድንበሯን ቆርሶ በመስጠትና ሰፋፊ ለም መሬቷን ዜጎችን በማፈነቀል ለዉጭ ባለሀብቶች በኪራይ ( ሊዝ ) ስም በመሸጥ ላይ ይገኛል ። በዚህም ድርጊቱ የአካባቢዉን ኗሪወች ከቀያቸዉ በማፈናቀል ለርሀብ ለስደትና ለሞት እንዲዳረጉ አድርጓል ። ይህ እቅድ ከሃያ አምስት አመት በፊት የወጣና ዉጤቱም ከጎረቤት ሃገራት ጋር የነበረንን መልካም ግንኙነት የሚያደፈርስና ለማያባራ ጦርነት የሚዳርግ በመሆኑ ሁሉም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ተድራጅቶ ሊያወግዘዉና ሊታገለዉ ይገባል ።

ሀገራችን በእድሜዋና በታሪኳ አይታዉ ከማታዉቀዉ ከዚህ ብሄራዊ ዉርደት ለመታደግ ይህ ከፋፋይ ዘረኛና ጎጥኛ መንግስት ለመጨረሻ ጊዜ ከስልጣን መወገድ አለበት ።ይህንም ተግባራዊ ለማድረግ ድርጅትና ትግል የሂደቱ ድርና ማግ ናቸዉ ።በመሆኑም እኛ በኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ ስር የተደራጀን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያን ትግሉ የሚጠይቀዉን መስዋእትነት ለመክፈልና ከሁሉም በሀገር አንድነት አምነዉ በጋራ ለመስራት ከሚፈልጉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር አብሮ ለመታገል ህዝባችንን ለማስተባበርና ለድል ለማብቃት ዝግጁ መሆናችንን እናስታዉቃለን ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ

nile@epnp.info or nile.epnp@gmail.com